# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

30




ሐምሌ ፲፭ — ፲፱፻፸፱ ዓ. ም.

## ርእሰ አንቀጽ

# አድኀሪዎችና የተራማጆች ኅብረት

በተራማጅ ኃይሎች መሀከል ልዩነቶች በተነሱ ቁጥር አድኀሪዎች መሀል እየገቡ ይፈተፍታሉ ። አንዳንድ የዋሆች ታዲያ «በኛ መሀከል እነሱ ምን አገባቸው» በማለት ሲያስተጋቡ ይሰማሉ ። ነገር ግን ነገሩን ጠለቅ ብሎ ላየው ሰው አድኀሪዎች በኛ መሀል አይግቡ ማለት የመደብ ትግል አያካሂዱ እንደማለት የሚቆጠር የዋህነት ነው ። የመደቦች ትግል ተፋፍሞ በተለይ ደግሞ እንደዛሬዪቱ ኢትዮጵያ የጦፈ አብዮት በሚካሄድበት ወቅት አድኀሪዎችና ተራማጆች «አትድረሱብን አንደርስባችሁም» የሚባባሉ አይደሉም ። እንዲያውም እያንዳንዱ ሰፈር ትግሉን ፈር ለማስያዝና በድል አድራጊነት ለመውጣት ሲል የራሱን ኃይል የማጠናከሩ ታክቲክ የትግሉ ግማሽ አካል ብቻ ነው ። ግማሹ ትግል በጠላት ሰፈር ገብቶ ያንን ጠላት ውስጥ ውስጡን መቦርቦር ፤ በዚያ ሠፈር ውኅንብር መንዛት ፤ የዚያን ሰፈር ኃይል መከፋፈልና ማድከም እንደሆነ እየተደጋገመ የተነገረ ጉዳይ ነው ።

የኢትዮጵያ አብዮታውያን ትግላቸውን ከግቡ በማድረስ ዛሬ በፀረ ፊውዳል ፀረ ኢምፔሪያሊስት ፀረ ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት መድረክ ላይ ሊሰበሰቡ የሚችሉትን ኃይሎች በሙሉ በአንድነት መሰብሰብና ማደራጀት እንዳለባቸው ያውቃሉ ። በአንፃሩ ደግሞ ፀረ አብዮት ኃይሎች ራሳቸውን በማደራጀትና በማጠናከር ሳይቆጠቡ የአብዮቱን ሰፈር ለመቦርቦር ለማዳከምና አንድነቱን እንዳያጠናክር ለማድረግ እንደሚሰሩ ይገነዘባሉ ። ስለአድኀሪዎችና የተራማጆች ኅብረት በምናነሳበት ወቅት መነሳት ያለብን ከዚህ መሠረታዊ ሐቅ ነው ። አድኀሪ ኃይሎች የተራማጆች ኅብረት ቢመሠረት አይወዱም ። ባለ ኃይላቸው ሁሉ ይህንን ኅብረት በእንጭጩ ለመቅጨት ይሞክራሉ ።

አድኀርያን አብዮቱን ለመቃወም ከይፋ አመጽ አንስቶ እስከ ሰርጎ ገቦች ረቂቅ ተንኮል እንደሚጠቀሙ ሁሉ የተራማጆችን ኅብረት ለመቋቋምም እንደዚሁ ፊት ለፊት ከመጋፈጥ አንስቶ ለኅብረትና ለአንድነት ተቀርቋሪ ሆኖ እስከመቅረብ ድረስ ባለው የፀረ ሕዝብ ትግል ሰንሰለት ይጠቀማሉ ። ይፋውን አመጽ እንተወውና ወደአልተነቃበት የሰርጎ ገቦች ሴራ እናተኩር ።

የተራማጆችን ኅብረት ለማደናቀፍ አድኀሪዎች በአብዮቱ ሰፈር ሰርገው በመግባት የኅብረት ተቆርቋሪ መስለው ብዙ ጥፋት ሊያደርሱ ይችላሉ ። እንደሁኔታውም በልዩ ልዩ ታክቲኮች ይጠቀማሉ ። በአንድ በኩል መሠረተ ቢስ የሆኑ « ልዩነቶች » እንዲጐሉና ተራማጆችን እንዲያቃቅሩ ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በመሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ያሉ ልዩነቶች እንዲድበሰበሱና በአሸዋ ላይ የተገነባ «አንድነት» እንዲመሠረት ይታገላሉ ።

አድኀሪዎች ልዩነቶች እንዲጐሉ ያደርጋሉ ሲባል ልዩነቶችን ማድበስበስ ለአንድነት ጥሩ ነው ማለት እንዳልሆነ ግልጽ መሆን አለበት ። በዚህ በኩል ማርክሲዝም ሌኒንዝም ከውሀ የጠራ አቋም አለው ። የጠነከረ አንድነት ሊመሠረት የሚቻለው በታጋዮች መሀል ያሉት የልዩነት ነጥቦች በሚገባ ጐልተው ሲታዩና መስመሮች ጥራት ባለው ሁኔታ ተለይተው ሲታዩ ነው ። እንዲያውም ለጠነከረ አንድነት የሚታገሉ አብዮታውያን በታጋዮች መሀል ያሉት ልዩነቶች ፤ እነሱን ከሌሎች የሚነጥላቸውን መስመር አንጠርጥረው ለሰፊው ሕዝብና ለሌሎች ታጋዮች አሳይተው ለመስመራቸው መታገላቸው ተገቢና አስፈላጊ ነገር ነው ። አለበለዚያ በተድበሰበሰ «የመስመር አንድነት» ላይ የተመሠረተ ኅብረት በአሸዋ ላይ እንደተሰራ ቤት እንደሚሆን ጥርጥር የለውም ። ስለሆነም አድኀሪዎች ልዩነቶችን ያጐላሉ በሚባልበት ጊዜ የአባባሉን ትርጉም ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል ።

አድኀሪዎች በተራማጆች መሀል አሉ የሚሏቸውን ልዩነቶች አጉልተው ለማሳየት የሚሞክሩት በመሀከላቸው መራራቅንና መጣላትን ለመፍጠር ነው ። ስለሆነም የሚያነሷቸው ልዩነቶች በተራማጆች መሀል መነሳት ካለባቸው የመስመር ልዩነቶች ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የላቸውም ። አድኀሪዎች የሚጠቁሟቸው «ልዩነቶች» በሀቅ ላይ ሳይሆን በአሉባልታ ላይ የተመሠረቱ ናቸው ። በተገለጸ አቋም ላይ ሳይሆን ባልተባለና ባልተነገረ አቋም ላይ ናቸው ። አንገብጋቢ በሆኑት የአብዮቱ ጥያቄዎች ላይ ያሉትን ልዩነቶች ሳይሆን ከተያዘው ትግልና ካሉት የመስመር ትግል ነጥቦች ጋር እምብዛም ግንኙነት በሌላቸው ጉድለቶች ላይ ነው ። አድኀሪዎች አጉልተው ለማሳየት የሚፈልጉት እነዚህን «ልዩነቶች» ነው ።

እንዲያውም የባሰ አለ ። አድኀሪዎች በዚህ ብቻ አይቆጠቡም ። አብዮታውያን እነዚህን መሠረተቢስና ፍሬቢስ «ልዩነቶች» ችላ ብለው መሠረታዊ በሆኑ የአብዮቱ አንገብጋቢ ጥያቄዎች ላይ ሲያተኩሩና በነሱ ላይ ይፋ የሆነ ውይይት እንዲካሄድ ሲሞክሩ አድኀሪዎች ታክቲክ ለውጠው ይመጣሉ ። ይኸኔ ደግሞ እነሱ ፤ አድኀሪዎቹና ሰርጎገቦቹ ለተራማጆች ኅብረት ተቆርቋሪ ሆነው ልዩነቶችን ይፋ ማውጣትና «ለጠላት» ማሳየት አስፈላጊ ስላለመሆኑ አስተማሪዎች ሆነው ብቅ ይላሉ ። እዚህም ላይ ዓላማቸው ግልጽ ነው ። ውስጥ ውስጡን አሉባልታ እየነዙ ፤ መሰረተቢስ የሆኑ ልዩነቶችን እየፈጠሩ የተራማጆችን ኅብረት ለመቦርቦር ይጥራሉ ። በሃቀኛ አቋም ላይ መሠረታዊ በሆኑ ልዩነቶች ላይ የሚደረጉትን ይፋ የሆኑ ክርክሮችን ግን የአብዮታውያንን ሰፈር ስለሚያጠናክሩባቸው ይፈሯቸዋል ። ይቃወሟቸዋል ።

ስለሆነም አድኀሪዎች የተራማጆችን ኅብረት ለመቋቋም የሚጠቀሙበትን የረቀቀ ታክቲክ ለመቋቋም አብዮታውያን በአንድ በኩል የነሱን አሉባልታና መሠረተቢስ «ልዩነቶች» ፋርሽ ማድረግ በሌላ በኩል ደግሞ አድኀሪዎች ከጦር የሚፈሩትን ለተራማጆች ኅብረት መጠናከር ፍቱንና ሳይንሳዊ የሆነ በአብዮቱ አንገብጋቢ ጥያቄዎች ላይ የሚደረግ የመስመር ትግልን ማካሄድ አለባቸው ።

ለዚህ ደግሞ ዛሬ በኢትዮጵያ አመቺ ሁኔታ አለ ። የኢትዮጵያ ተራማጆች በሙሉ ሊሰበሰቡበት የሚችሉበት መድረክ አለ ። ይኸውም የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ነው ። እንደዚሁም የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒንስቶች ኅብረት የፈጠሩበትና የትግላቸው መመሪያ የሆነ መርሐ ግብር አውጥተዋል ። ማርክሲስት ሌኒንስቶች የፈጠሩት ኅብረት ይህንን መርሐ ግብር ከሥራ ላይ ለመዋል ለመታገል ግልጽ በሆነ መድረክ ላይ የፈጠሩት የትግል ኅብረት ነው ።

ይህ መርሐ ግብር ለአድኀሪዎች ምንም ገብቶ የመፈትፈቻ ቀዳዳ ሊሰጣቸው አይገባም ። እያንዳንዱ ማርክሲስት ሌኒንስት ቡድን መታየት ያለበት ማርክሲዝም ሌኒንዝምን መመሪያ በማድረግ ፤ ይህንንም ሳይንስ ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ወዶና ፈቅዶ ለተቀበለው መርሐ ግብር ከሚያሳየው ታማኝነት አንፃር ነው ። እያንዳንዱ ቡድን ሐቀኛ የሚባለው ይህ መርሐ ግብር

ከሥራ ላይ ስለሚውልበት ሁኔታ ልዩነቶች ሲነሱ እነሱን በሃቅና በጥሞና እየተነተነ የሌሎችን አቋም ሳያጣምም የራሱን አቋም ሳያጋንን በሰፊው ሕዝብ ፊት የርእዮተ ዓለም ትግል ለማካሄድ የደፈረ እንደሆን ብቻ ነው ።

አንድ ቡድን ይህንን ካደረገ በእውነት ለተራማጆች ኅብረት ሠራ ማለት ነው ። ይህንን ትቶ ግን ልክ አድኃሪዎች እንደሚመኙት በማርክሲዝም ሌኒንዝምን ካልተመራ የገባለትን ዓላማ ረግጦ በመርሐ ግብሩ ላይ የተዘረዘሩትን ዓላማዎች ለመፈጸም በሃቅ ካልታገለ ፤ ይህ መርሐ ግብር በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ከሥራ ላይ ስለሚውልበት ዘዴ በሰፊው የኢትዮጵያን ሕዝብ ፊት በየጊዜው ሐሳቡን ለመስጠትና ከሌሎች የትግል ጓዶቹ ጋር ያለውን ልዩነት አንጠርጥሮ ለማሳየት ካልደፈረ ይህ ቡድን ወደደም ጠላም የኢትዮጵያን አብዮት ወደፊት ለማራመድ የረባ ትግል አካሄደ ማለት አይቻልም ።

ስለሆነም ኅብረት የፈጠሩት ማርክሲስት ሌኒንስት ቡድኖች በሚተቹበት ወቅት በመርሐ ግብሩ መሠረት የወዝ አደሩን ፓርቲ ለመፍጠር ከቡድን ስሜት ርቀው ይታገላሉ ወይስ አይታገሉም ? ሰፊውን ሕዝብ ለማንቃት ፤ ለማደራጀትና ለማስታጠቅ ይታገላሉ ወይስ አይታገሉም ? ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ እንዲለቀቁ ይታገላሉ ወይስ አይታገሉም ? አድኃሪው ቢሮክራሲ እንዲወገድና በሱ አንፃር ደግሞ ሕዝባዊ ድርጅቶችና ሕዝባዊ አስተዳደር ከቢሮክራሲው ቁጥጥር ሥር ወጥተው እንዲያብቡ ይታገላሉ ወይስ አይታገሉም ? በመርሐ ግብሩ ላይ እንደተጠቀሰው ሰፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ለረዥም ጊዜና የተወሳሰበ ትግል ያዘጋጃሉ ወይስ የአጭር ጊዜ ድል ይመኛሉ ? ሰፊውን ሕዝብ በራሱ እንዲተማመን ይቀሰቅሱታል ወይስ አይቀሰቅሱትም ? ከሁሉ በላይ ደግሞ ልክ አድኃሪዎች እንደሚመኙት እነዚህን ሊያከራክሩ የሚችሉ ነጥቦች ትተው በተራማጆች መሐል አሉባልታ ይነዛሉ ወይስ በየጊዜው በነዚህ ጥያቄዎች ላይ ይፋ የሆነ አቋም እየወሰዱ የተራማጆች ኅብረት ከብረት እንዲጠነክር ይታገላሉ ?

ኅብረቱን ለማጠናከር የሚፈልግ ሐቀኛ አብዮታዊ ሁሉ ራሱን መጠየቅ ያለበት እነዚህን ጥያቄዎች ነው ። ኅብረቱ እንዲጠናከር ወደውሕደት ተለውጦ ለአብዮታችን እጅግ አስፈላጊ የሆነው የወዝ አደር ፓርቲ እንዲመሠረት ከላይ በጠቀስናቸውና ሌሎች የአብዮቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ሰፊና ይፋ የሆነ ውይይት ያስፈልጋል ። ይህ ካልተደረገ ውይይቶች በነዚህ መሠረታዊ ነጥቦች ላይ ካላተኮሩ ወይም ከታፈኑ ለአብዮታችን አደገኛ ነው ። ልክ አድኃሪዎች እንደሚመኙት ጉልተው የሚታዩት « ልዩነቶች » በአሉባልታ ላይ የተመሠረቱ ፍሬ ቢስ ልዩነቶች ብቻ ይሆናሉ ፤ አለ የሚባለው አንድነት ልዩነቶች ተንጠርጥረው ሳይሆን ተድበስብሰው የሚታፈኑበት መሠረት የሌለው አንድነት ይሆናል ። እንደዚህ ከሆነ በሰፊራችን ሠርገው የገቡት አድኃሪዎች በርግጥ ለጊዜውም ቢሆን ፀረ አብዮት ተልእኳቸውን ፈጸሙ ማለት ነው ይህ እንዳይሆን መታገል የእያንዳንዱ አብዮታዊ ቡድንና ግለሰብ የተቀደሰ ተግባር ነው ።

የአድኃርያን ሤራ ይከሽፋል !
የተራማጆች ኅብረት ይጠነክራል !!

የ ጊ ዜ ው   ጥ ያ ቄ

# የጊዜው ዋነኛ ቅራኔ የትኛው ነው ?

ከአባይነህ አብተው

በማንኛውም ሁኔታና ወቅት የሚኖረው አንድ ዋና ቅራኔ ብቻ ነው ። ሌሎች በኅብረተ—ሰቡ ውስጥ ያሉ ቅራኔዎች ሁሉ የሁለተኛ ደረጃ ቅራኔዎች ናቸው ። በዚህ ዋና ቅራኔ መፈታትም እነ ዚህ ሌሎች ቅራኔዎች መፍትሔ ያገኛሉ ። ነገር ግን ፤ ጉዳዩ እንዲህ እንደሚያዩት ቀላል አይደለም አብዮታዊ ሁኔታ እጅግ የተወሳሰበ ስለሆነ ፤ ነገ ሮች ደግሞ በጣም የተያያዙ ስለሆኑ ፤ ሁልጊዜ ከሚታዩት ጉልህ ቅራኔዎች ዋነኛው የትኛው ነው የሚለውን ጥያቄ በቀላሉ መመለስ ይቻላል ማለት አይደለም ። ብዙ ጊዜ ፤ ግለሰቦች ብቻ ሳይሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች በዚህ ጥያቄ ላይ እየተሳሳቱ በአብዮታቸው ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሰዋል ። ዋና ቅራኔ የትኛው ነው የሚለውን ጥያቄ ለመመ ለስ አስቸጋሪ ከሚያደርጉት ምክንያቶች አንዱ ዋናውን ቦታ የያዘው ቅራኔ ቦታውን ለቆ ፤ በአ ንድ የተወሰነ ወቅት በሌላ ዋና ቅራኔ ሊተካ መቻሉ ፤ ወይንም ደግሞ በሁለተኛ ደረጃ ላይ ይገኝ የነበረ አንድ ቅራኔ በተቀየረ ሁኔታ ከዋናው ቅራኔ ጋር መዳበል መቻሉ . . . ነው ። ስለሆነም የጊዜው ዋና ጠላት ማነው የሚለውን ጥያቄ እንደያው መጺሐፍት ከሚሰጡት ምሳሌ ብቻ ወይንም ላይ ላዩን በሚታዩ ክንውኖች ብቻ ለመ መለስ መሞከር ከስህተት ላይ ይጥላል ። ቆም ብሎ ተጨባጭ ሁኔታን አጥንቶ ፤ የላይ ላይ ክንውኖችን ብቻ ሳይሆን ውስጣዊ ይዘታቸውንና ግንኙነታቸውን መርምሮ የጊዜው ዋና ጠላት ማነው የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ መነሳት ያስፈ ልጋል ። በዛሬው ሁኔታ የጊዜው ዋና ጠላት ማነው የሚለውን ጥያቄ ወደመመለሱ ሳንሄድ ፤ በአብዮታችን ሂደት የጊዜው ዋና ጠላት በሚለው ጥያቄ ላይ ተራማጅ መሰል አወናባጆች ያቀረቡት ትንታኔ በሀቀኛ ተራማጆች ትግል ባይከሽፍ ኖሮ ምን ያህል አብዮታችንን ሊያስቀለብስ ይችል እን ደነበረ እንመልከት ። ይህንን የምናደርገው ቁል ቢዎች በጊዜው ዋና ጠላት ላይ የሚፈጥሩትን ውዥንብር ጉጂነት ለማሳየት ብቻ ሳይሆን፤ ተራማጆ ችም ሳያውቁት ወይንም በስሜታዊነት በጊዜው ዋና ጠላት ጥያቄ ላይ ቢሳሳቱ አብዮቱን እንደሚ ጐዳ ለማሳየት ጭምር ነው ።

በተለይ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ተራ ማጅ እርምጃዎችን መውሰድ እንደጀመረና በዚ ህም ከኢትዮጵያ አብዮት መሠረታዊ ጠላቶችና ከአብዮቱ ሂደት ከተንሸራተቱ ከሃዲዎች ጋር ከከ ፍተኛ ቅራኔዎች ውስጥ እንደወደቀ ፤ በደርጉና በሰፊው ሕዝብ መሃል የነበረው ቅራኔ በሕዝብ መሃል እንዳለ የሚቆጠር ቅራኔ ሆኖ ነበር ። ዳሩ ግን ፤ « ኢ. ሕ. አ. ፓ.» የተባለው ፀረ — አብዮት ቡድን «ደርግ ፋሽስት ነው ፤ ዋና ጠላት ነው » የሚል መስመር ይዞ ታገለ ። ይህን መስመር ሰፊው ሕዝብም ቢቀበለው ኖሮ (ደግሞ ከንቃት ዝቅተኛነት የተነሳ ወጣቱና ወዝአደሩ ተቀብሎት ነበር ) ምን ዓይነት የኃይሎች አሰላለፍ ያስከትል ነበር ? ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥትና በአብዮቱ ውስጥ ደርጉ የያዘውን ቦታ የተረዱ ሀቀኛ ተራማጆች ባንድ ወገን ፤ ሰፊው ሕዝብ ፤ የኢትዮጵያ አብ ዮት መሠረታዊ ጠላቶችና ከአብዮቱ የተንሸራተቱ ክፍሎች በሌላ ወገን ተሰልፈው በተፋጩና ደር ግና ተራማጆች ለብቻቸው ተነጥለው በተመቱ ነበር ። እንዲህ ዓይነቱን አሰላለፍ ያስቀረው ባንድ በኩል ደርጉ በተጨባጭ ተራማጅ እርምጃዎች ተቀዳሚ የሕዝብ ጠላት አለመሆኑን ማስመስከ ሩና ሀቀኛ ተራማጆችም የጊዜው ዋና ጠላት ደርግ እንዳልሆነ በማሳየት ያደረጉት የፖለቲካ መስመር ትግል ናቸው ። በዚህ የአብዮቱ ዋና ጠላት ማነው ? በሚለው ጥያቄ ላይ የተገኘው ጥራት ፤ በጠቅላ ላው በአብዮቱ ሰፈር ለተገኘው ጥራትና አብዮትና ፀረ—አብዮት ኃይሎች በግልጽ በተለዩበት የዛሬው አሰላለፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ።

ሁለተኛው ምሳሌ ደግሞ ፤ ከጥቂት ወራት በፊት ሴራቸው በከሸፈባቸው በነ ዓለማየሁ ኃይሌ የቀረበው የጊዜው ዋና ጠላት ትንተና ነው ።

መለስ ብለን ያየነውን ሁኔታ ስንመለከት ፣ ባንድ በኩል የውስጥ ጠላቶች መንሸራተት ፀረ—አብዮት ትግል ማፋፋም በግልጽ ይታይ ነበር ። ይህ የቅልበሳ ሴራ ደግሞ ታች ታቹን በግልጽ ፀረ ሕዝብ አመጽ ላይ የተሰማሩት አድኃርያን ሴራ ብቻ ሳይሆን ከላይም በደርግ ውስጥ በነበሩ ቀኝ ኃይሎችና በአድኃሪ ቢሮክራቶች የተደገፈ ነበር ። በሌላ በኩል ደግሞ የውጭ ጠላቶች አብዮቱን ከበው ማስፈራሪያ ይሰነዝሩ የነበሩበት ፣ ለውስጥ አድኃሪዎች የሞራልና የማቴሪያል ድጋፍ የሚሰጡበት ወቅት ነበር ። አብዮቱ በውጭ ጠላቶች ከበባ ቢጨነቅም ከቅልበሳ አፋፍ ያደረሰው የውስጥ ጠላቶች መጠናከርና ትግል ሆኖ ሳለ ፣ እነዓ ለማየሁ ኃይሌ «በውጭ ጠላቶች ከበባና በኢትዮጵያ ሕዝብ መሃል ያለው ቅራኔ ዋነኛው ነው» የሚል ትንተና ይዘው ቀረቡ ። በትንተና ብቻ አልተወሰነም ፣ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ በውስጥ ጠላቶች ላይ ያነጣጠረውን ጦር ለማዶልዶም የሰፊውን ሕዝብ ትግል ማፈን ፣ የተተፉ አድኃሪዎችን አንስቶ ማቀፍ ያዙ ። እነርሱ በነደፉት መስመር ስር ሰፊው ሕዝብ ቢሰለፍ ኖሮ ፣ ያኔ እንደተባለውም ፣ እርሱ ኬላ ኬላዋን ሲያይና ሲጠብቅ የውስጥ ጠላቶች አብዮቱን ከጀርባ ወግተው በቀለበሱለት ነበር ። በወቅቱ ከደርግ ውስጥና ውጭ የነበሩ ተራማጆች የጊዜው ዋና ቅራኔ በውስጥ አድኃሪዎችና በአብዮቱ ኃይሎች መሃል ያለው ቅራኔ እንደሆነ ፣ ከ፲ ኪሎ ሜትር መትረየስ ደግኖ ከሚጠብቅ ጠላት ላይ ለመድረስ ፣ ከ፩ ሜትር ርቀት ሽጉጥ ይዞ ሊገድል የሚያደባን ጠላት መደምሰስ እንደሚያስፈልግ ለማሳየት በመቻላቸው የነዓለማየሁ መስመር ተሸነፈ ። እርሱም ብቻ ሳይሆን ፣ ከዚህ መስመራቸው ጋር ተያይዞ የነበረው የቅልበሳ ሴራቸው በተወሰደባቸው ቁርጠኛ እርምጃ ከሸፈ ።

እነዚህ ሁለት ምሳሌዎች ፣ የአብዮቱን ቋንቋ የሚናገሩ ጠላቶች በዋና ቅራኔ ጥያቄ ላይ በማወናበድ ምን ያህል የአብዮቱን ዕድል ከአደጋ ላይ ሊጥሉ እንደሚችሉ ያሳየናል ። ወደአሁኑ ሁኔታ እንምጣና ፣ በዛሬው የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የጊዜው ዋነኛ ቅራኔ ፣ የርሱ መፈታት ለኢትዮጵያ ዕድገት ወሳኝ የሚሆነው ቅራኔ የትኛው ነው ? ይህን ጥያቄ ለመመለስ ከመሞከራችን በፊት ለዚህ መልስ ሊኖሩ የሚችሉ ሁለት የተለያዩ አስተያየቶችን እንመልከት ።

አንደኛው ስህተተኛ አስተያየት ፣ ልክ እንደነ ዓለማየሁ ኃይሌ ጊዜ ሁሉ ፣ ዛሬም የጊዜው ዋና ቅራኔ በውስጥ ጠላቶች ብቻና በአብዮቱ ኃይሎች መሃል ያለው ቅራኔ ነው የሚለው ነው ። ይህ አስተያየት ባንድ በኩል የነዓለማየሁ ሴራ መመታት ያስከተለውን ለውጥ ያልተረዳ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ከነዓለማየሁ ኃይሌ ሴራ መመታት በኋላ የሰፊው ሕዝብ ትግል ያገኘውን መጠነኛ የደረጃ እድገት ያላጤነ ነው ። በመጠኑ እና ብራራው ። የነዓለማየሁ ኃይሌ መመታት ፣ የኢትዮጵያ አድኃሪዎች ከላይ አብዮቱን ለመቀልበስ ያደረጉትን ሙከራ ለጊዜውም ቢሆን መክሸፍ ያመለክታል ። በዚህም ከውጭ ሆነው የኢትዮጵያን ፀረ—አብዮት ኃይሎች በመርዳት የውጭ ጠላቶች የቅልበሳ መሳፈያቸው ተጐድቷል ። ከነዓለማየሁ መመታት በኋላ በተፈጠረው ምቹ ሁኔታ ሰፊው ሕዝብ የተወሰነ የትጥቅ ኃይል አግኝቷል። ለተወሰነ ጊዜ በወሰዳቸው ነፃ እርምጃዎች የውስጥ ጠላቶችን ኰርኩሟል ። ይህም ብቻ ሳይሆን እስካሁን ካደረገው በበለጠ የውስጥ ጠላቶቹን ለመምታት ተነስቷል ። የውስጥ ጠላቶቹን በየቀኑ ለኰፍ ከማድረግ ይልቅ ፣ ይበልጥ ተዘጋጅቶ ዶጋመድ ሊያደርጋቸውም ይፈልጋል ። እነዚህ ሁሉ ባሁኑ ጊዜ የውስጥ ጠላቶቹን ምንም እንኳ የውጭ ጠላቶች ርዳታ ባይጐድላቸውም በዚህ ርዳታ ብቻ በራሳቸው ለመቆም ከሚያስችላቸው ደረጃ ላይ እያደረሳቸው ነው ። ስለሆነም በውስጥ ጠላቶች ብቻና በሰፊው ሕዝብ መሃል ያለው ቅራኔ የጊዜው ዋነኛ ቅራኔነቱ እየቀነሰ መጥቷል ።

ሁለተኛው ስህተተኛ አስተያየት ደግሞ ፣ የጊዜው ዋነኛ ቅራኔ በውጭ ጠላቶችና በኢትዮጵያ ሕዝብ መሃል ያለው ቅራኔ ነው የሚለው ነው፣ ይህ ስህተተኛ አስተያየት ባንድ በኩል በውስጥ ጠላቶች ላይ የደረሰውን ጥቃት ከመጠን በላይ የሚያጋንን ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የውጭ ጠላቶችን መሠረታዊ ዓላማ የውስጥና የውጭ ጠላቶችን ግንኙነት በፍጹም ያልተረዳ ነው ።

የውስጥ ጠላቶችን በሚመለከተው በኩል ፣ አንደኛ ዛሬም በሚገባ የተጠናከሩበት ፣ ከአብዮቱ ኃይሎች ገና የማያዳግም ሞት ያላገኙበት አካባቢ ብዙ ነው ። የነሱ መመታት በተጀመረበት አካባቢ እንኳ የአካባቢው ሰፊ ሕዝብ ገና በሚገባ ስላልነቃ ፣ ስላልተደራጀና ስላልታጠቀ ፣ እነዚህን ጠላቶች መደምሰሱ ብቻ ሳይሆን የአካባቢውን ሰፊ ሕዝብ በሚገባ ለማንቃት ለማደራጀትና ለማስታጠቅ የሚደረገው ትግል ወይ ገና አልተጀመረም ፣ ወይ በመጀመር ላይ ነው ። የኢትዮጵያ አድኃሪዎች የቅልበሳ መሠረት የሆነው ከኃይለሥላሴ የተወረሰ ግድንግድ ቢሮክራሲ አድኃሪ ጉኑ ገና አልተመታም ። ይህ ሁሉ የሚያሳየን የውስጥ አድኃሪዎች «ምን ተነኩና» ባያሰኝም ገና አብዮታችን ብዙ የሚጋተራቸው ጠላቶች መኖራቸውን ነው ።

ሌላው ነጥብ ደግሞ ፣ የውጭ ጠላቶች በተለይ ኢምፔሪያሊስቶች ከኢትዮጵያ ምን ይፈልጋሉ ? የሚለውን ጥያቄ ስንጠይቅ ምናልባትም የኢትዮጵያን ግዛት ቆርሳ ለመውሰድ ከምትሻው ሱማሌ በስተቀር አብዛኞቹ ከኢትዮጵያ ድንበር ገፍተው መሬት ለመያዝ ዓላማ የላቸውም እነርሱ የሚፈልጉት የኢትዮጵያን አብዮት መቀልበስን ፣ የኢትዮጵያን አድኃሪዎች መልሶ ከመንግሥት ሥልጣን ማድረስን ነው ። አንዳንድ ሰዎች ፣ ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ የደረሰውን የውጭ ኃይሎች ጣልቃ ገብነት በቻይና ከደረሰው የጃፓን ወረራ ጋር ያመሳስሉታል ። ይህ ግን ስህተት ነው ። የጃፓን ኢምፔሪያሊዝም ዋና ዓላማ ቻይናን በቅኝ ግዛት ለመያዝ እንጂ በቀጥታ የቻይናን አብዮት ለመቀልበስ አልነበረም ።

የጃፓን የወረራ መሣሪያ የራስዋ ወታደሮች እንጂ ከአንዳንድ ከሃዲዎች በስተቀር በመሠረቱ የቻይና አድኃሪዎች አልነበሩም ። በኢትዮጵያ ውስጥ ግን ከሁለቱም ነጥቦች አንፃር ለየት ያለ ነው ። የኢትዮጵያ የውጭ ጠላቶች ዋና ዓላማ ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛት ማድረግ ሳይሆን የኢትዮጵያን አብዮት ማስቀልበስ ነው ። ሁለተኛ በደቡብ ከሚታዩት ሰርጎገቦች በስተቀር ፣ የውጭ ጠላቶች ዋና መሣሪያዎች የውስጥ አድኃሪዎች ማለትም ኢ.ዲ.ዩ. ኢ.ሕ.አ. ፓና ኢ.ኤል.ኤፍ ናቸው። እስካሁን ካልነው የሚከተለው ደግሞ ፣ ባሁኑ ወቅት በውጭ ጠላቶችና በአብዮት ኃይሎች ብቻ መሃል ቅራኔ ዋነኛው ቅራኔ እንዳልሆነ ያሳየናል።

እንግዲህ ፣ በውስጥ ጠላቶችና በአብዮት ኃይሎች ፣ በውጭ ጠላቶችና በአብዮት ኃይሎች ሁለቱም ለየብቻ ተወስደው የጊዜው ዋነኛ ቅራኔ አይሆኑም ካልን ፣ ታዲያ የጊዜው ዋነኛ ቅራኔ የትኛው ነው ማለት ነው ? እስካሁን ከዘረዘርነው ለዚህ ያለን መልስ ግልጽ ይመስለናል ። የጊዜው ዋነኛ ቅራኔ ፣ የውስጥና የውጭ ጠላቶች በጥምር ባንድ በኩል ፣ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሌላ በኩል መሃል ያለው ቅራኔ ነው ።

ይህም ማለት የውስጥና የውጭ ጠላቶች ፍጹም ከመቀራረባቸው የተነሳ ፣ በውስጥና በውጭ ጠላቶች መሃል ፍጹም የሆነ የዓላማና የትግል መተሳሰር ስላለ ፣ ሁለቱ በማይነጣጠል መልክ ከአንድ ወገን ቆመው ፣ የእናት አገሩን ዳር ድንበርና አንድነት ብቻ ሳይሆን የመራራ ትግሉን የድል ፍሬዎች ላለማስነካት የሚታገለው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሌላ ወገን ቆሟል ማለት ነው ። እንደዚህም መሆኑ እነዚህን ፣ ማለትም የውስጥና የውጭ ጠላቶች ነጣጥለን ተመልክተን የትግል ታክቲክ ብንነድፍ ከስህተት ላይ እንወድቃለን ፣ አብዮታችንንም ከበለጠ ማጥ ውስጥ እንከታለን ። ዛሬ አንዱን ነገ ሌላውን ካልን ፣ ዛሬ እንታገለዋለን ካልነው ጠላት ጋር ስንዋደቅ ለነገ ያስቀመጥነው ከላያችን ላይ ይወጣል ። በሌላ አነጋገር ፣ የውስጥ ጠላት ብቻ ዋና ነው ብለን ከርሱ ጋር እዚህ ስንተናነቅ የውጭ ጠላቶች ያጠቁናል ። ግን ደግሞ የውጭ ጠላት ብቻ ዋና ነው ብለን ኬላ ኬላው ላይ ስናፈጥ የውስጥ ጠላት ጠልፎ ይጥለናል ።

ይህንን የጊዜው ዋነኛ ቅራኔ የትኛው ነው የሚለውን ነጥብ በይበልጥ ግልጽ ለማድረግ ታላቁ ማኦ ስለዚሁ ነገር ከሰጡት ትምህርት በመጠኑ ተርጉመን እንጥቀስ ።

«በእንደዚህ ዓይነት ሀገር (ማለትም በከፊል ፊውዳልና ከፊል ካፒታሊስት አገር) ኢምፔሪያሊዝም የወረራ ጦርነት በሚጀምርበት ጊዜ ፣ ከአንዳንድ ከኃዲዎች በስተቀር የሀገሪቱ የተለያዩ መደቦች ከኢምፔሪያሊዝም ጋር በሚደረገው ብሔራዊ ጦርነት በጊዜያዊነት ሊተባበሩ ይችላሉ ። በእንዲህ ዓይነት ጊዜ በኢምፔሪያሊዝምና በሀገሪቱ መሃል ያለው ቅራኔ ዋነኛ ሲሆን በሀገሪቱ ውስጥ ባሉት የተለያዩ መደቦች መሃከል ያለው ቅራኔ በሙሉ (በፊውዳሉ ሥርዓትና በሰፊው ሕዝብ መሃል የነበረውን ዋነኛ ቅራኔም ጨምሮ) ለጊዜው ወደ ሁለተኛና ተከታዩ ቦታ ይቀየራል። በቻይና የ፲፰፻፴፱ው የኦፒየም ጦርነት ፣ የ፲፰፻፺፬ቱ የቻይናና ጃፓን ጦርነት ፩. . . የዛሬው (፲፱፻፴፯) የቻይናና የጃፓን ጦርነት ለዚህ ምሳሌ ናቸው ።

ግን በሌላ ሁኔታ ቅራኔዎች ቦታቸውን ይለውጣሉ ። ኢምፔሪያሊዝም ጭቆናውን የሚያካሂ

ደው በጦርነት ሳይሆን ለስለስ ባሉ ዘዴዎች ፤ በፖለቲካዊ ፤ ኢኮኖሚያዊና ባሕላዊ በሚሆንበት ጊዜ ፤ በከፊል ቅኝ ግዛት ሀገሮች ያሉ የገዥ መደቦች ለኢምፔሪያሊዝም አሻቸውን ይሰጡና ሁለቱ በሰፊውን ሕዝብ አብረው ለመጨቆን አንድነትን ይመሠርታሉ ። በእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ሰፊው ሕዝብ ብዙውን ጊዜ ኢምፔሪያሊዝምንና የፊውዳሉን መደቦች ኅብረት በመቃወም ወደሲቪል ጦርነት ያመራል ኢምፔሪያሊዝም ደግሞ ብዙውን ጊዜ ከፊል ቅኝ በሆኑ አገሮች ያሉት አድኃሪዎች ሕዝቡን እንደጨቆኑ በቀጥተኛ ድርጊት ሳይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ ይረዳል ። ስለዚህም በሀገር ውስጥ ያሉት ቅራኔዎች በተለይ ይከራሉ ።

አብዮታዊ የሲቪል ጦርነት የኢምፔሪያሊዝምንና የቡችሎቹን ፤ የውስጥ አድኃሪዎችን ሕልውና ከአስጊ ደረጃ ሲያደርስ ፤ የበላይነቱን ለማቆየት ኢምፔሪያሊዝም ብዙውን ጊዜ በሌሎች ዘዴዎች ይጠቀማል ። ወይ አብዮታዊውን ግንባር ከውስጥ ለመከፋፈል ይሞክራል ፤ አለበለዚያም የውስጥ አድኃርያንን በቀጥታ ለመርዳት የታጠቁ ኃይሎችን ይልካል ። በእንደዚህ ዓይነቱ ጊዜ የውጭ ኢምፔሪያሊዝምና የውስጥ አድኃሪዎች በአንድ ጫፍ ሰፊው ሕዝብ በሌላ ጫፍ ይሆኑና በነዚህ መሃል ያለው ቅራኔ ዋነኛው ይሆናል ። የሌሎች ቅራኔዎች እድገት በዚህ ዋነኛ ቅራኔ ይወሰናል ፤ ወይንም ሌሎቹ ቅራኔዎች ሁሉ በዚህ ዋነኛ ቅራኔ ተጽእኖ ስር ይወድቃሉ ። ከ(፲፱፻፲፯ቱ) የጥቅምቱ አብዮት በኋላ በተለያዩ የካፒታሊስት ሀገሮች ለሩሲያ አድኃርያን የተሰጠው ርዳታ ለትጥቅ ወረራ ምሳሌ ነው ። በ፲፱፻፳፯ የሻንግካይ ሼክ ክህደት የአብዮታዊ ግንባር መከፋፈል ምሳሌት ነው ።

(ማኦ ሴቱንግ ምርጥ ሥራዎች ቅጽ ፩ ፤ ገጽ ፫፻፴፩—፫፻፴፪ ትርጉም የግል)

ከዚህ ረዥም ጥቅስ ሦስት ሁኔታዎችን እንረዳለን ፤

፩ኛ/ ባጠቃላይ በአንድ አገር ሕዝብና በኢምፔሪያሊዝም መሃል ያለው ቅራኔ ዋነኛ ቅራኔ የሚሆንበት ሁኔታ ፤

፪ኛ/ በሀገር ውስጥ አድኃሪዎችና በሰፊው ሕዝብ መሃል ያለው ቅራኔ ዋነኛ የሚሆንበትን ሁኔታ፤

፫ኛ/ የውጭ ኢምፔሪያሊዝምና የውስጥ አድኃሪዎች ባንድ ወገን ሰፊው ሕዝብ በሌላ ወገን ሆኖ በሁለቱ መሃል ያለው ቅራኔ ዋነኛው ቅራኔ የሚሆንበት ሁኔታ ፤

ከጥቅሱ በፊት ካብራራነውና ጥቅሱም እንደሚያሳየን በአገራችን ያለው የጊዜው ዋነኛ ቅራኔ ይኸ ሦስተኛው እንደሆነ መረዳቱ ቀላል ነው ። ይህን ከተረዳን ደግሞ ፤ ሁለት መሠረታዊ ጥንቃቄዎችን ማድረግ ይኖርብናል ።

ሀ/ ዛሬ የአገራችንን ዳር ድንበርና አንድነት ላለማስደፈር የምናካሂደው ትግልና ባጠቃላይ አብዮቱን ከቅልበሳ ለማዳንና ከግብ ለማድረስ የምናካሂደው ትግል ፍሬም የማይነጣጠሉ መሆናቸውን ።

ለ/ የአገራችንን ዳር ድንበርና አንድነት ላለማስደፈር በሚደረገው ትግል ሀቀኛ ተሳታፊ የሚሆኑት በአብዮቱ መቀልበስ የሚጐዱ በአብዮቱ ከግብ መድረስ ጥቅም የሚያገኙ የኢትዮጵያ ጭቁን መደቦችና የኅብረተ—ሰብ ክፍሎች ብቻ እንጂ በስመ ኢትዮጵያዊ ማንም እንዳልሆነ።

እነዚህን ሁለት ነጥቦች ከተረዳን የአብዮቱ ወዳጆች በዚህ የአገርን ዳር ድንበርና አንድነት የማስጠበቅና አብዮቱን ከቅልበሳ የማዳን ትግል የሚኖራቸውን የተያያዙ ተግባሮች በሚገባ ለመተለም እንችላለን ። ለዚህም በአብዮትና በፀረ—አብዮት መሃል ካለው የኃይል ሚዛን አንጻር ኢትዮጵያን ለሦስት ከፍለን ብንመለከት የሚከተሉት ሦስት የተያያዙ ተግባሮች ግልጽ ይሆናሉ ።

ሀ/ ረዘም ካለ ጊዜ ወዲህ የአካባቢው ጭቁኖችና ተራማጅ ኃይሎች ባካሄዱት የከረረ ትግል የኃይሉ ሚዛን ለአብዮቱ ኃይሎች የሚያደላባቸው አካባቢዎች ፤ በነዚህ አካባቢዎች ጠላት አልቀለታል በሚል ግምት አጉል መዝናናት እንዳይመጣ ፤ ይህ የኃይል ሚዛን ለአብዮቱ ወገኖች እንዳደላ እንዲቆይ ከፍተኛ የማጠናከር ትግል መካሄድ አለበት ። የነዚህ አካባቢዎች መጠናከር ከውስጥና ከውጭ ጠላቶች ጋር ለሚካሄደው የከረረ ትግል እነዚህን አካባቢዎች የአብዮቱ ደጀን ያደርጋቸዋል ።

ለ/ የአብዮትና ፀረ—አብዮት ኃይሎች ከፍተኛ ግብግብ የያዙባቸውና አንደኛውም ያላሸነፈባቸው አካባቢዎች ፤ በተለይም በነዚህ አካባቢዎች ፀረ—አብዮት ኃይሎችን ማሸነፍ የውስጥ አድኃሪዎችን የጀርባ አጥንት እንደመስበር ይቆጠራል ። ስለሆነም ፤ ምንም እንኳ ከውጭ ጠላቶች ጋር የተፋጠጥንበት ሁኔታ ውስጥ ብንገኝም ፤ በነዚህ አካባቢዎች ካሉ የፀረ አብዮት ኃይሎች ጋር ያለውን ትግል በፍጹም ችላ ማለት የለብንም ። የሞትና የሽረት ትግሉ ቀጥሎ የኃይሉ ሚዛን ለአብዮት ኃይሎች እንዲያዳላ መደረግ አለበት ። ለዚህም በነዚህ አካባቢ ያሉትን የአብዮት ኃይሎች በይበልጥ ማንቃትና ማደራጀት በተለይም በይበልጥ ማስታጠቅ ያስፈልጋል ። ዲስፕሊን በተሞላበት ነፃ ሕዝባዊ እርምጃዎች የአብዮቱ ኃይሎች የፀረ—አብዮቱን ሰፈር ለመደምሰስ የሚያደርጉት ትግል መታገዝ አለበት ።

ሐ/ የውስጥ አድኃሪዎች በቀጥታ በውጭ ጠላቶች እየታገዙ የተጠናከሩበት ፤ የአብዮቱ ወገኖች ወይንም ከመደብ አንፃር ከአብዮቱ ጋር መሰለፍ ያለባቸው ኃይሎች ደካማ የሆኑባቸው አካባቢዎች ። በነዚህ አካባቢዎች የሚደረገው ትግል ከታጠቁ የውስጥ ጠላቶችና በተዘዋዋሪ መንገድ ከውጭ ጠላቶች ጋር የሚደረግ ትግል ነው ። በሀ-ና በለ የጠቀስናቸው ተግባሮች ችላ ሳይባሉ ፤ አሁን የተያዘው አብዮታዊ ዘመቻ በነዚህ አካባቢዎች በወታደራዊና በፖለቲካ ትግል ፀረ—አብዮት ኃይሎችን ለመደምሰስ ከአብዮቱ ጐን መሰለፍ ያለባቸውን የአካባቢው ኃይሎች ለማቀፍ የመረረ ተጋድሎ መደረግ ይኖርበታል።

በፖለቲካው በኩል ፤ በነዚህ አካባቢዎች የሚያወናብዱ የታወቁ ፀረ—አብዮት ኃይሎችን ለአካባቢው ሰፊ ሕዝብ በማጋለጥ ፤ የኢትዮጵያን አብዮት ሂደት ፤ ምንነትና ግብ በማስረዳት የአብዮቱ የሩቅ ተመልካች ሳይሆኑ ቀጥተኛ ተሳታፊ ለመሆን የሚያስችለውን ንቃት እየሰጡ ማደራጀት ። ይህም ባንድ ወገን የታጠቁት ጠላቶች በማስፈራራትና በማወናበድ የያዟቸውን ኃይሎች ከነርሱ እጅ ማስወጣት እነርሱን የሚያዳክም ሲሆን ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ዞሮ ዞሮ የአብዮቱን ሰፈር ባጠቃላይ የሚያጠናክርና በዚህ አካባቢ ያሉ ፀረ—አብዮተኞችን ለመቋቋም የሚችል የአካባቢውን አብዮታዊ ኃይል መፍጠር ነው ።

ጠላቶች ባየሉባቸው የአብዮቱ ኃይሎች ደካማ በሆኑባቸው አካባቢዎች የሚጠበቀው ወታደራዊ ተግባር ግልጽ ቢሆንም ፤ አንደኛ ከላይ ከጠቀስነው ፖለቲካዊ ተግባር ጋር መያያዝና እርሱንም መረዳት ይኖርበታል ። ሁለተኛም ፤ ዘማቹ ሠራዊት ከላይ ያልነውን የፖለቲካ ተግባር ሊያሟላ የሚችለው ራሱ ስለተግባሩ በሚገባ ሲያውቅ ስለሆነ ፤ በዚሁ አንፃር አብዮታዊ አሠራርን ተከትሎ አብዮታዊ ጉቃቱ ማደግ ይኖርበታል ።

እናጠቃል ። ባሁኑ ወቅት በአገራችን ያለው ዋነኛ ቅራኔ በውስጥና በውጭ ጠላቶች ባንድ በኩልና በሰፊው ሕዝብ በሌላ በኩል መሃል ያለው ቅራኔ ነው ። ይህን ቅራኔ ለመፍታት አንድ ላይ የሚሄዱ ሦስት የተያያዙ ተግባሮች መሟላት አለባቸው ። እነርሱም የአብዮቱ ኃይሎች ከአብዮቱ ጠላቶች ጠንክረው በሚገኙባቸው ቦታዎች ይህ የአብዮቱ ኃይሎች ጥንካሬ እንዳይላላ ይበልጥ እንዲጠናከር መታገል ፤ የአብዮቱ ኃይሎችና የአብዮቱ ጠላቶች ባልተሸናነፉባቸው እንደ አዲስ አበባ ባሉ አካባቢዎች ደግሞ የአብዮቱ ኃይሎች እንዲያሸንፉ የነዚህን አካባቢ ፀረ አብዮት ኃይሎች ለመመንጠርና ለማዳከም የሚደረገውን ትግል ማፋፋም።ከውጭ ጠላቶች ጣልቃ ገብነት ጋር በተያያዘ ሁኔታ የውስጥ ጠላቶች በተጠናከሩባቸው አካባቢዎች ደግሞ የተጀመረው ዘመቻ የነዚህን አካባቢዎች ሰፊ ሕዝብ ከአብዮቱ ሰፈር በማያስገባ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ትግል የውጭ ጠላቶችን ለመቋቋምና የታጠቁ የውስጥ አድኃሪዎችን ለመደምሰስ መታገል ።

ለነዚህ የተያያዙ ተግባሮች መከናወን ሁኔታውን ለማመቻቸት የሚያስፈልጉ እርምጃዎች (የቢሮክራሲው መመታት ጉዳይና የዲሞክራሲያዊ መብቶች) ጥያቄ አሉ ። እነዚህን በሌላ ጽሑፍ እንመለስባቸው ይሆናል ። እስከዚያው ድረስ ግን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ነፃነትና አንድነት ፤ ለኢትዮጵያ አብዮት ግስጋሴ የሚቆረቆሩ ዜጎች ሁሉ የዛሬውን ዋነኛ ቅራኔ ተረድተው ፤ እነዚህን የተያያዙ ፤ ለቅራኔው መፈታት አማራጭ የሌላቸው ተግባሮች ለማከናወን መነሳት ይኖርበታል ። በተለይም ሀቀኛ ተራማጆች የዚህን ቅራኔ ምንነትና የሚፈታበትን አብዮታዊ መንገድ ለሰፊው ሕዝብ በማስተማር ፤ በአብዮታዊ ትግሉና ተሳትፎው የእናት አገሩን ሕልውና የሚፃረሩትን ፤ በመራራ ትግሉ የተቀዳጃቸውን ድሎች ሊነጥቁት ያሰፈሰፉትን የውስጥና የውጭ ጠላቶች እንዲደመስስና የራሱን ዕድል ሙሉ ለሙሉ በጁ ለማስገባት እንዲበቃ ለማስቻል በግንባር ቀደምትነት መሰለፍ አለባቸው ።

ፊውዳሊዝም፤ኢምፔሪያሊዝምና ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም ይውደሙ ፤ ፤

በነቃ በተደራጀና በታጠቀ የሰፊው ሕዝብ አመጽ የውስጥና የውጭ ጠላቶች የተጣመረ አድኃሪ አመፅ ይደመሰሳል ፤